# ትግል ስንል! ትግል ሲሉ!

(ግጥም ከዓሊ ሁሴን)

አበቃቀላችን ለየቅል፣
በስመ ተክል ዱባና ቅል!
ትግል ሲሉ፣ ትግል ስንል!!

ትግል ስንል
ትግል ሲሉ፣
ስንወጥር
ሲያላሉ፣
ስንገምድ
ሲተረትሩ፣
ስንራመድ
ሲያስመትሩ፣
ስንሰበስብ
ሲበትኑ፣
ስናቀጣጥል
ሲያዳፍኑ፣
ትግል ሲሉ እነሱ! መቆም የናፈቁ!
በዳዴ የሚሄዱ!
ከዋናው ጠላት ይልቅ፣
ወዳጅ የሚያጠቁ! ወዳጅ የሚጎዱ!!

***

ትግል ስንል እኛ ገና ከጅምሩ፣
የዘውድን አገዛዝ ከነ ጥንብሩ፣
ዳግም ላይነሳ በአመፅ ስንገረስስ፣
ለጥቆ የመጣውን ደም የጠማን ፋሽስስት፣
በሕይወት የተጋፈጥን ያለምንም ስስት!!
ትግል ስንል እኛ!
ሳልስ የገጠመንን፣
ይህን አፍን አውሬ ወያኔን ዘረኛ!
እስኪወገድ ድረስ!
የማንበረከክ ፍፁም የማንተኛ!!

***

ትግል ሲሉ እነሱ!
እንደ ኩባንያ ሙሉ መድህን ያለው፣
መታሰር መገረፍ ስደት የማይቀምሰው፣

ከውስጥም ከውጭም ሞት ፍርድ የማይኖረው፣
ታፍኖ መወሰድ ወፌ-ይላላ የሌለው፣
ደቂቃና ሰዓት የድል ቀን ወስነው፣
ዕቁብ እየጣለ እንደሚጠብቅ ሰው!!
ትግል ሲሉ እነሱ በፈገግታ ብቻ ዱላ ሳያነሱ፣
ነጭ ጨርቅ አራግበው ጠላትን ሊያፈርሱ!
ትግል ሲሉ እነሱ አረንጓዴ እና ነጭ፣
ዝና የሚያለብሳቸው ገንዘብ የሚያመነጭ!

***

ትግል  ስንል እኛ፣ ግም ሥርዓት ልንለውጥ!
ሳይሆን በልመና! ሳይሆን በልምጥምጥ!
እኛ!!
ትግል ስንል፣ ነጭ ሰማያዊ፣ ጥቁር ቀይ ቅልቅል!
በሥጋ ዝምድና የማይቆም በክልል!!
እየታገሉ ሞት! እየሞቱ ትግል!!
ጠላትን ከወዳጅ ለይቶ የሚጥል!
ታግሎ አታጋይ ስንል!!
ከትላንትም በስቲያ ትላንትም ይፈጠር፣
ያልነበረ እንዳለ በአዲሱም ይዋቀር!
እኛ ትግል ስንል!!
የሥርዓት ለውጥ እንጂ!  መቼ ለበርጩማ?
ልደታን ልንቆጥር ገብተን ከፓርላማ?!!!

***

ትግል ሲሉ እነሱ!
ታግለን ከጣልነው ጋር ያኔ የወደቁ!
በዳዴ የሚሄዱ፣ መቆም የናፈቁ፣
የፋሽስት መሃረብ ሆነው ያገለገሉ!
በተገኘው ገዢ መሃላ ‘ሚምሉ!
ዘረኛን ለመጣል ዘረኛ ሰብስበው፣
አላላውስ ማለት መድረኩን አጣበው!!
ትግል ሲሉ እነሱ፣ ለሄደው ለመጣው እያጎነበሱ!
ሲተቹ የሚያብዱ፣ የሚያለቃቅሱ!!
ሳይታገሉ ሞተው፣ ስድስት ወር ሳይደርሱ!
ረዥም ዕድሜ ቆዩ፣ ብለው የሚያለቅሱ!!!